ኢትዮጵያዊነት፡- የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ
ETHIOPIAWINNET: COUNCIL FOR THE DEFENSE OF CITIZEN RIGHTS
www.ethiopiawin.net
ECDCR P.O Box 171, East Lansing, MI 48823

November 12, 2020

# በትግራይ ክልል ሕግን ለማስከበር እየተወሰደ ስላለው እርምጃ ፤

በማንኛውም ሀገር መንግሥት የሕዝቡን ሰላም መጠበቅና የሕግ ማስከበር ተግባሮቹ ተቀዳሚ ኃላፊነቱ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም ላለፉት ሁለት ዓመታት የብሔርና ሃይማኖት ተኮር ወንጀሎች በተለያዩ ክልሎች በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ሲፈፀሙ መንግሥት ኃላፍነቱን በሚገባ አልተወጣም የሚሉ ወቀሳዎች ከሕዝብ ሲቀርቡ ቆይተዋል፡፡

አንዳንድ የትግራይ ክልል መሪዎች በሠሩት ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው ለፍርድ እንዲቀርቡ መጥሪያ ቢሰጣቸውም እስከ አሁን በእምቢተኝነት ቆይተዋል። አልፎ ተርፎም በሀገራችን የብሄር ግጭቶች እንዲፈጠሩና አለመረጋጋት እንዲፈጠር በቀጠሯቸው የጥፋት ኀይሎች አማካኝነት ሲያስፈጽሙ በማስረጃ እየተያዙ ነው፡፡ አሁን ደግሞ በእነዚሁ መሪወች አማካኝነት በሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ አሰቃቂ ግድያዎች ፈጽመዋል፡፡ ይህ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ሃገራዊ ክህደት ነው። መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ወንጀለኞቹን ከሕግ ፊት ለማቅረብ እየወሰደ ያለውን እርምጃ እንደግፋለን፡፡ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብም ድጋፉን እየሰጠ ይገኛል፡፡

ካሁን ቀደም እንደገለፅነው፣ አሁን በትግራይ ክልል አመራሮች ላይ የሚካሄደውን የሕግ ማስከበር ዘመቻ በጥሞናና በጥንቃቄ እንዲከናወን፣

- መንግሥት ጥፋተኞችን ለሕግ ለማቅረብ በሚያደርገው ዘመቻ ሰላማዊ ሕዝቡ እንዳይጎዳ እስካሁን እያደረገ ያለውን ጥንቃቄ እያደነቅን ለወደፊቱም በዚሁ እንዲቀጥል እናበረታታለን፡፡

- አንደኛው የችግሩ ምንጭ በየክልሉ የተዋቀረው አላስፈላጊ 'ልዩ ኀይል' መሆኑ ታውቆ የየክልሉ "ልዩ ኃይሎች" ከመከላከያ ሠራዊትና ከፌደራል ፖሊስ ውስጥ እንዲጠቃለሉ የሚያስችል እርምጃ ባስቸኳይ እንዲወሰድ እናሳስባለን፡፡

- የሃይማኖት አባቶች፤ የሀገር ሽማግሌወች፣ አባገዳዎች፣ የሲቪል ማኅበራትና የሚድያ ኃላፊዎች ሁሉም ለሰላምና ለሕግ መከበር ተከታዮቻቸውን እንዲያስተምሩ አጥብቀን እናሳስባለን፡፡

- በኅብረተሰባችን መሀከል እስከአሁን የመከፋፈል፤ የእርስ በርስ ጦርነትና ጥላቻን በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ የሚያደርገው በሌሎች ሀገሮች ታይቶ የማይታወቀው በህወሃት፤ በዚሁ ወንጀለኛ ቡድን፤ የተቀነባበረው ዘርና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት መሆኑ ታውቆ በአስቸኳይ እንዲታረም ወይም በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ እንዲደረግ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

**ኢትዮጵያ በነፃነቷና ባንድነቷ ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ኢትዮጵያዊነት፤ የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ**